# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 295 ታህሳስ 25 2006 ገጽ 1


የወያኔ "አንድ ለአምስት" የኑሯችን አካል እየሆነ መጥቷል። በአንዳንድ ቦታዎች አለመደራጀት ሥራ የሚያሳጣ እየሆነ ነው። በማናቸውም ምክንያት ራሳቸውን ወያኔ ጉያ ውስጥ ያገኙ የሕዝብ ወገኖች ካሁን በኋላ መሥራት ያለባቸው ወያኔን ከውስጥ ሆኖ የማዳከምን ሥራ ማፋጠን ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ "አንድ ለአምስት" አመቺ የሆነ መዋቅር አይገኝም

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## አዲስ አበባ ዉስጥ ወያኔ ገድሎ የቀበራቸዉ ሰዎች የጅምላ መቃብር ተገኘ

ባለፈዉ ሳምንት ታህሳስ ሃያ አንድና ሃያ ሁለትና አርብና ቅዳሜ እለት ከስድት ኪሎ ወደ ፈረንሳይ በሚወስደው መንገድ ላይ በሚገኘው የጃንሜዳ ጦር ካምፕ (በቀድሞ ስሙ ሦስተኛ ሻለቃ) ግቢ ውስጥ ቁጥራቸዉ ወደ 6 የሚጠጉ አስከሬኖች በብርድልብስ እንደተጠቀለሉ ተቀብረዉ ተገኝተዋል። አስከሬኖቹ የተገኙት ለመንገድ ስራ ሲባል የጦር ካምፑ ግቢ አጥር ወደ ውስጥ ፈርሶ ሲቆፈር እንደሆነ ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና ያስረዳል። የአይን ምስክሮች እንደተናገሩት ቦታዉ በመቆፈሪያ ማሽኖች በመቆፈር ላይ እያለ በመጀመሪያ ሁለት አስከሬኖች በብርድልብስ እንደተጠቀለሉ ተንከባለዉ ወደላይ ሲወጡ ያዩና በሁኔታዉ የተደናገጡት ቆፋሪዎች ስራቸን አቋርጠዉ ይሄዳሉ። ሰራተኞቹ በነጋታው ቅዳሜ እለት ረፋዱ ላይ በሌላ አቅጣጫቁ ፋሮ ሲያደርጉ አሁንም እንደገና በተመሳሳይ ሁኔታ በብርድ ልብስ የተጠቀለሉ አራት አስከሬኖች አግኝተዋል። ይህ አስደንጋጭ ዜና በአካባቢዉ ሲሰማ ከጦር ካምፑ ዉስጥ የተወሰኑ ወታደሮችና ከፍተኛ መኮንኖች ከፍተኛ ወደ ቦታው በመምጣት ስራው እንዲቆም ትእዛዝ አስተላልፈዉ በአካባቢው የነበረው ሰው ከቦታው በፍጥነት እንዲባረር ትዕዛዝ ሰጥተዋል። በስፍራው ተገኝተው ሁኔታውን ሲከታተሉና የክፍለ ከተማዉ ነዋሪዎች ፎቶ ለማንሳት ጥረት ቢያደርጉም በወታደሮቹ ከመከልከላቸዉም በላይ አንዳንዶቹ የእጅ ስልካቸዉንና ካሜራቸዉን ተቀምተዋል። አስከሬኖቹ የተጠቀለሉበት ብርድልብስ ቀለሙንና ይዞታዉን ሳይቀይርና ሳይበሰብስ መገኘቱ የጅምላ ግድያው በወያኔ ዘመን የተፈጸመ ለመሆኑ ማስረጃ ነዉ ሲሉ ሁኔታዉን በቅርበት የተከታተሉ የአይን እማኞች ተናግረዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ በመዋቅር ስም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የደብር ሃላፊዎችንና ሠራተኞችን ሊያባርር መሆኑ ተሰማ

በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የውስጥ አሰራር ውስጥ ጣልቃ በመግባት፤ ላለፉት 22 ዓመታት ስርአተ ቤተክርስቲያንን ያለ እረፍት ሲበጠብጥ፣ ፓትሪያርክና ጳጳሳትን ሲሾምና ሲሽር፣ ከቤተክርስቲያኒቱ አሰራር ውጭ እንደፈለገ ሁሉንም ሲያተራምስ የነበረው ፋሽስት ወያኔ፤ ሰሞኑን ደግሞ ራሱ ባዘጋጃቸውና ማንነታቸው ያልተገለጹ የኮሚቴ አባላት አማካኝነት ተዘጋጅቶ ቀረበ በተባለ የአስተዳደር ሰራተኞች መዋቅር ሰበብ ነባር ሰራተኞችን ለማፈናቀል ዝግጅቱን ማጠናቀቁ ተሰማ።

በዚህ የመዋቅር ደንብ መሰረትም የቤተክርስቲያኒቱ የአሰራር ደንብ ከሚጠይቀው ውጭ የወያኔ ተላላኪዎችንና ጉዳይ አስፈጻሚዎችን የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ እና ዲፕሎማ ነው በሚል ሰበብ ሆን ብሎ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ክፍል ለመሰግሰግ መታቀዱም ተሰምቷል። ዜናው ገና ከመሰማቱም የየሀገረ ስብከቱ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ሰራተኞች በኩል ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳስነሳ እየተዘገበ ይገኛል።

የቤተክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ሳይወያዩበትና ከተለመደው አሰራሯ ውጭ ሊጸድቅ የተዘጋጀውን የአስተዳደር መዋቅር እንቃወማለን የሚሉ በአዲስ አበባ የሚገኙ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ሰራተኞች "መዋቅር ተብየው ከመጽደቁ በፊትም ሊቃውንትና የሚመለከታቸው አካላት በከፍተኛ ሁኔታ ሊወያዩበትና ሊያዳብሩት ይገባል" እያሉ ይገኛሉ። ፋሽስት ወያኔ በቤተክርስቲያኒቱ ላይ ላለፉት ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ እየተከተለ ያለውን ትክክለኛ ያልሆነና ፖለቲካን ቀዳሚ ያደረገ አካሂያድ እናውቃለን የሚሉ ወገኖች ግን "ወያኔ ከቤተክርስቲያኒቱ ቃለ አዋዲ ውጭና የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ አካል ከሆነው ከሲኖዶሱ እውቅና ባፈነገጠ መልኩ ብዙ ህገ ወጥ አሰራሮችን እንዳጸደቀና ተፈጻሚ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው ይህ የሰሞኑ የአስተዳደር መዋቅርም ምንም እንኳ ብዙ ተቃውሞ የሚሰማበት ቢሆንም መጽደቁ አይቀርም" ይላሉ። ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት ከቤተክርስቲያኒቱ ሲኖዶስ እውቅናና ስምምነት ዉጭ በፓትሪያሪክ ላይ ፓትሪያርክ መሾምን ጨምሮ በቤተክርስቲያኒቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ግድያ እስከመፈጸምና ጳጳሳትን እያሰደደ እስከመደብደብ የደረሰ የማፍያ ስራ ሲሰራ እንደነበር በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል።

## በደቡብ ሱዳን ዉስጥ አሳቢ አጥተዉ የሚጨነቁት ወገኖቻችን ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ ተነገረ

ለፖለቲካ ፍጆታ እንጅ ለወገን እምብዛም ክብር የሌላቸው የወያኔዎቹ ሃይለማሪያም ደሳለኝና ቴዎድሮስ አድሃኖም ሰሞኑን የተፈጠረውን የደቡብ ሱዳን ግጭት ምክንያት በማድረግ ላይ ታች እያሉ ባሉበት ባሁኑ ወቅተ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ኢትዮጵያዊያን ግን በደቡብ ሱዳን መውጫ አጥተው በርሃብና በውሃ ጥም እየተሰቃዩ መሆናቸው ተሰማ። በደቡብ ሱዳን የሚገኙት የኑዌርና ዲንካ ጎሳ አባላት ግጭት እኛንም ያሰጋናል የሚሉት እኒሁ ኢትዮጵያዊያን፤ ርዳታ እንዲደርስላቸውና ወደ ሀገራቸው እንዲመልሳቸውም ፋሽስት ወያኔን በከፍተኛ ሁኔታ እየተማጸኑ ቢሆንም የደቡብ ሱዳኑን ግጭት በመፍታቱ ሂደት ላይ ተሳታፊ ከሆኑት የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የመሪነቱን ቦታ በመጨበጡ ላይ ጊዜያቸውን እያጠፉ ያሉት ወያኔዎች ግን ጆሮ እየሰጧቸው እንዳልሆነ እየተወሰደ ካለው ደካማ ርምጃ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ በፊት የሕዝብ ጩኸትን፣ የጋዜጠኞችና የሚመለከታቸው ሰዎች ቅድሚያ ጥቆማን ከምንም ባለመቁጠርና በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን መከራ እጅግ በጣም በማቅለል ዘግይቶ የተንቀሳቀሰው ፋሽስት ወያኔ በወገኖቻችን ላይ ለደረሰው አንገት የሚያስደፋ አሳፋሪ ውርደትና ሞት ምክንያት መሆኑን የሚያስታውሱ ወገኖች፤ በደቡብ ሱዳን እየተሰማ ካለው የወገኖቻችን ሞትና ስቃይ በመነሳት የሳውዲ አረቢያው አይነት በደቡብ ሱዳንም እንዳይደገም ስጋታቸውን ይገልጻሉ። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አክራሪዎቹ የህወሃት አባላት የመከላከያ አዛዥነቱ ከህወሀት እጅ እንዳይወጣ እየጣሩ ነዉ

ስልጣን የኛ ብቻ ነዉ ብለዉ የሚያምኑት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የአገር መከላከያ ዋና አዛዥነቱ ቦታ ከትግሮኛ ተናጋሪዎች እጅ እንዳይወጣ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን በመከላከያ ውስጥ ከሚገኙ ወታደራዊ አዛዦች የተገኘዉ መረጃ አመለከተ። አክራሪና ዘረኛ የሆኑት የህወሃት ባለስልጣናት ጄኔራል ሳሞራ የኑስን ለመተካት ከሁሉም በላይ የተሻለ ቦታ ላይ የነበሩትን ጄ/ል አበባው ታደሰን ሰበብ አስባብ በመፈለግ አድማ ለማድረግ አሰበዋል ብለዉ ሃላፊነታቸዉ እንዲቀነስና ጀኔራሉ ከውድድር ውጭ እንዲሆኑ ማድረጋቸዉን የመከላከያ ምንጮቻችን ገልጸዋል። ይህንን የህወሀቶችን አድማ በማስተባበርና በመምራት ጄኔራል ሞላ ሀይለማርያምና ጄኔራል ሰአረ መኮንን ዋና ዋናዎቹ መሆናቸዉ ታዉቋል።

ሶስቱ ጄኔራሎች ማለትም ጄ/ል አበባው ታደሰ፤ ጄኔራል ሞላ ሀይለማርያምና ጄኔራል ሰአረ መኮንን "ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በመከላከያ ውስጥ ያለውን ሙስና ለመከላከል ብቃቱ ጎሏቸዋል በሚል እንደተነጋገሩና ጉዳዩ በወታደራዊ ደህንነት መምሪያ ክፍል ሲታይ ቆይቶ በመጨረሻም ይፋ ተደርጎ" ሶስቱም ጄኔራሎች በያዙት ማእረግ ሃለፊነታቸው ቀንሶ እንዲሰሩ እንደተወሰነባቸዉ የሚታወስ ነዉ። ይሁን እንጅ ጄ/ል ሞላ እና ጄ/ል ሳህረ ከጄኔራል አበባው ጋር በአድማው የተሳተፉት ሆን ተብሎ ጄ/ሉን ከስልጣን ተፎካካሪነት ለማስወጣትና ፍትሀዊ ውሳኔ የተላለፈ መሆኑን ለተቀሩት የሰራዊቱ አባላት ለማሳየት መሆኑን ወታደራዊ ምንጮች ገልጸዋል። ጄ/ል ሳሞራን ይተካሉ ተብለው ከሚጠበቁት ጄኔራሎች ዉስጥ በቅርቡ የሌ/ጄ ማእረግ ያገኘዉ ጄ/ል ዮሃንስ ገብረመስቀል ቀዳሚዉ እንደሆነ ወታደራዊ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

## የወያኔ ዘረኞች በሶስት ድርጅቶች ላይ ሌላ አኬልደዳማ እየሰሩ ነዉ ተባለ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር የሚታገሉ ድርጅቶችን ስምና ዝና ለማጉደፍ የሚያደርገዉን የቀበፀ ተስፋ መፍጨርጨር በመቀጠል ከዚህ ቀደም ሰርቶ ህዝብ የቀለደባቸዉን "አኬልደማንና" "ጂሀዳዊ ሀረካትን" የመሰለ ሌላ የቴሌቪዥን ድራማ እየሰራ መሆኑን ለስርዐቱና ለድራማዉ ዝግጅት ቅርበት ያላቸዉ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ተናገሩ። ዉስጥ አዋቂዎቹ የመረጃ ምንጮቻችን በሰጡን መረጃ መሰረት በመሰራት ላይ ያለው አዲስ ፊልም አነግን ፤ ኦብነግና ግንቦት ሰባትን በሽብርተኝነት የሚያወግዝ ነው።

ወያኔ ከዚህ በፊት የሰራቸዉ ድራማዎች ህዝባዊ ተቀባይነት እንዳላገኙ እያወቀ በአሁኑ ወቅት እንዲህ አይነቱን ድራማ ለምን መስራት እንደፈለገ ግልጽ የሆነ ነገር ባይኖርም የስርዐቱን ከፍተኛ ባለስልጣኖች ጨምሮ ብዙዎች በግልጽ እንደሚናገሩት ወያኔ ካላይ ስማቸዉ በተጠቀሰዉ ሦስት ድርጅቶች እንቅስቃሴ ክፉኛ እየተደናገጠ መሆኑን ለማወቅ አያዳግትም። ባለፉት ሁለት አመታት ወያኔ በተከታታይ የሰራቸዉ "አኬልደማ" እና "ጂሀዳዊ ሀረካት" ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔን "አንድ ለአምስቶች" ወያኔን ለማዳከም እንጠቀምባቸው

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመቆጣጠር እንዲያመቸው "በአንድ ለአምስት" እያደራጀው ነው። ይህ አደረጃጀት ስታሊን ለሠላሳ ዓመታት ሶቭየት ኅብረትን፤ ኤንቨር ሆዣ ደግሞ ለአርባ ዓመታት አልባኒያን ጠፍረው የገዙበት ስልት ነው። በዚህ የአገዛዝ ስልት መሠረት እያንዳንዱ ሰው በመዋቅር ተይዞ አራቱ ለአንዱ መረጃ የሚያቀብሉበት ሥርዓት ይዘረጋል።

ሕዝብን በድርጅት አባልነት ስም በመዋቅር ማስገባት ለአንባገነኖች የሚሰጠው ዋነኛ ጥቅም የማኅበረሰብን ስነልቦና መስበሩ ነው። ይህ አወቃቀር ዜጎች የአምባገነኑን መንግሥት ኃይል ከመጠን በላይ አግዝፈው፤ እራሳቸውን ደግሞ አንኳሰው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። ዜጎች፣ "መንግሥት እያንዳንዱን ነገር አብጠርጥሮ ያውቃል" በሚል የፍራቻ ቆፈን እንዲያዙ ያደርጋቸዋል። እያንዳንዱ ሰው ጓደኛውን እንዲጠረጥር በማድረግ አምባገነኖች የስለላ ተቋማቸዉ ጠንካራና ሁሉን-አዋቂ እንዲመስል ያደርጉታል።

ይሁን እንጂ የማኅበረሰብ ስነልቦና ካልተሰበረ፤ በፍራቻ ፋንታ በራስ መተማመን ከዳበረ ማንም ያደራጀው ማን ነፃ ህሊና ያላቸው አባላት ድርጅቱን ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ይጠቀሙበታል። አሁን በደረስንበት ሁኔታ ይህንን በአገራችን ተግባራዊ የማድረግ ሰፊ እድል አለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ፍራቻ እራሱን ነፃ እያወጣ ነው። ወያኔ ከስታሊንም ሆነ ከኤንቨር ሆዣ በተለየ መንገድ የአመለካከትና የርዕዮተዓለም ጉዳይ የሚያሳስበዉ ኃይል አይደለም። ቢያሳስበውም የሕዝብን ቀልብ የሚይይዝበት ምንም ነገር የለውም። ይህ ባህሪይዉ ነዉ ነው ወያኔ በእጅጉ የተጠላ ኃይል እንዲሆን ያደረገው።

እንዲህ በግዴታ እንጂ በእምነት ያልተሰባሰቡ ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ተመሳሳይ ፀረ-ወያኔ አቋም ያላቸው ሰዎች በአንድ "አንድ ለአምስት" ሕዋስ ውስጥ የመገኘታቸው አጋጣሚ የጎላ ነው። እነዚህ አባላት በግልጽ ከተነጋገሩበት ሕዋሱን ለፀረ-ወያኔ ትግል ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በመሆኑም ወያኔን ለመጨቆኛ መሣሪያነት ያዋቀረውን "አንድ ለአምስት" ራሱ ወያኔን መታገያ ብሎም ማዳከሚያ መሣሪያ ማድረግ ይቻላል። "አንድ ለአምስትን" በሽፋንነት በመጠቀም ውስጥ ውስጡን መጀራጀት በስፋት ልንይዘዉና ልንሰራበት የሚገባ ስትራቴጂ ነው።

የወያኔ "አንድ ለአምስት" የኑሯችን አካል እየሆነ መጥቷል። በአንዳንድ ቦታዎች አለመደራጀት ሥራ የሚያሳጣ እየሆነ ነው። በማናቸውም ምክንያት ራሳቸውን ወያኔ ጉያ ውስጥ ያገኙ የሕዝብ ወገኖች ካሁን በኋላ መሥራት ያለባቸው ወያኔን ከውስጥ ሆኖ የማዳከምን ሥራ ማፋጠን ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ "አንድ ለአምስት" አመቺ የሆነ መዋቅር አይገኝም።

በአሁኑ ሰዓት ግንቦት 7 ሕዋሳቶቹን በሁሉም ቦታ ለማዋቀር ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፤በዚህም መሠረት የግንቦት 7 ሕዋሶች በሁሉም የአገሪቱ አካባቢ ባልተማከለ መልኩ በብዛት እየተመሠረቱ ነው። ከዚህ ህዋሳቶችን ከመዘርጋት ሥራ ጎን ለጎን ህዝቡ በያለበት የወያኔን የራሱን መዋቅር በመጠቀም ወያኔንና ሥርዓቱን መገዝገዝ አለበት።

ይህንን ለማድረግ የግንቦት 7ን መመሪያ መጠበቅ አያስፈልግም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በራሱ መንገድ ተግባራዊ ሊያደርገው የሚችለዉ ነገር ነው።

በመሆኑም ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የወያኔ "አንድ ለአምስቶችን" ወያኔን ለማዳከም እንጠቀምባቸው የሚል ጥሪ ያቀርባል

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## አዲስ አበባ ዉስጥ ወያኔ ገድሎ የቀበራቸዉ ሰዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በአካባቢዉ ከተገኙ ወታደራዊ አዛዦች ዉስጥ አንደኛዉ ይህ ግቢ ሶስት ስርዓቶችን ያገለገለ በመሆኑ የማናቸው እንደሆነ ለማወቅ ባይቻልም፤ ሆኖም ሰዎች በመሆናቸው ክቡር ናቸውና አፈር አልብሷቸው ብሎ ትእዛዝ ሲሰጥ የሰሙ የአይን ምስክሮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መልዕክት ገልጸዋል። ሆኖም የደብረ ብርሀን ፋብሪካ ዉጤት ሆነዉ ብርድልብስ ምንም አይነት የመበላሸትና የመበስበስ ምልክት ሳያሳይ መገኘቱ ግድያዉ የቅርብ ግዜ ግድያ ነዉ የሚለዉን አባባል ያጠናክረዋል። የደርግ ስርዐት ከተደመሰሰ ሀያ ሦስተኛዉን አመት ሊያስቆጥር የቀረዉ አራት ወር ብቻ ሰለሆነ አፈር ዉስጥ የተቀበረ ብርድ ልብስ ይህንን ያክል ረጂም ግዜ ሳይበላሽ እንደማይቆይ በጉዳዩ ያናገርናቸዉ አክስፐርቶች ተናግረዋል።

## በደቡብ ሱዳን ዉስጥ አሳቢ አጥተዉ የሚጨነቁት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ምንም እንኳ ሞትን ጨምሮ የአካል ጉዳትና መጎሳቆል በደቡብ ሱዳን በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ቢሆንም እስካሁን ግን ከፋሽስት ወያኔ ይህ ነው የሚባል እገዛ እየተደረገላቸው እንዳልሆነ ከቦታው እየተሰማ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ምንም እንኳ የፋሽስት ወያኔ ቁንጮዎች ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ዘና ብለው እንደተቀመጡ ቢሆንም በሳውዲ አረቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ ሌላ ዙር አዲስ አፈሳና እንግልት መጀመሩ ተሰምቷል። ወገኖቻችንን ወደ ሀገር የማጓጓዝ እንቅስቃሴ ግን የለም በሚባልበት ደረጃ ላይ እንደሆነም ታውቋል። ባሁኑ ሰአት ከ80 እስከ 100 ሽህ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን በሳውዲ አረቢያ በስቃይ ላይ እንደሆኑ ይገመታል።

## የወያኔ ዘረኞች በሶስት ድርጅቶች ላይ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ድራማዎች ተቀባይነት አለማግኘታቸዉ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አገር ዉስጥም ካገር ዉጭም የቀለደባቸዉ ድራማዎች መሆናቸዉ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነዉ።

ባጭር ግዜ ዉስጥ ለህዝብ እንዲቀርብ በጥድፊያ እየተሰራ ባለው ፊልም ውስጥ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንም (ኢሳት) ለመወንጀል እየታሰበ መሆኑን ምንጮች አስታውቀዋል። ዘጋቢ ፊልሙ እስካሁን ባለመጠናቀቁ ና የመጨረሻውን የአርትኦት ይለፍ ባለማግኘቱ በይዘቱ ላይ ሙሉ አስተያየት ለመስጠት ባይቻልም የፊልሙ ዋና ዋና ኢላማዎች ግን ግንቦት 7፤ ኦነግ ፤ ኦብነግና ኢሳት መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል።

## የይርጋ ጨፌ መምህራን ወያኔን በመቃወም የስራ ማቆም አድማ አደረጉ

ደቡብ ክልል ይርጋጨፌ ከተማ ዉስጥ የሚገኙ መምህራን ገዢዉ ፓርቲ አለፈቃዳቸዉና አለፍላጎታቸዉ የሚጭንባቸዉን የገንዘብ መዋጮ በመቃወም የስራ ማቆም አድማ መጀመራቸዉን ጌዲኦ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። መምህራኑ አድማውን የጀመሩት የወያኔ አገዛዝ ያለፍላጎታችን ለአባይ ግድብ ማሰሪያ በሚል ሰበብ ደሞዛችንን እየተቆረጠብን ነው በሚል ነው። መምህራኑ ከሀምሌ 2005 ዓም ጀምሮ ለህዳሴዉ ግድብ ማሰሪያ እየተባለ ከደሞዛችን ላይ የሚቆረጠው ገንዘብ ከለፈቃዳችንና ዉዴታችን ነዉና ይቁም የሚል ደብዳቤ ለይርጋ ጨፌ ከተማ አስተዳደርና ለጌዲኦ ክልል ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት ጽፈዉ መላካቸዉ የሚታወስ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ታህሳስ አንድ ቀን 2006 ዓም በዞኑ መምህራን ማህበር ሰብሳቢነት የከተማው ከንቲባና የከተማው ትምህርት ዩኒት ሃላፊ በተገኙበት አቆራረጡ አግባብነት የሌለውና የመምህራንን መብት የጣሰ መሆኑ በውይይቱ ተረጋግጦ ከታህሳስ ወር ጀምሮ የሚቆረጠው ገንዘብ እንዲቆም፣ ተወስኖ ነበር። ነገር ግን የከተማው አመራር እንደተለመደው በመዋሸት እንዲቆም የተወሰነው ገንዘባችን እንዲቆረጥብን አድርጓል በማለት መምህራኑ የስራ ማቆም አድማ ጀምረዋል።

መምህራኑ በታህሳስ ወር የተቆረጠበን ገንዘብና ከሀምሌ 30፣ 2005 ዓም ጀምሮ በተከታታይ ለ5 ወራት የተቆረጠብን ገንዘብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲመለስልን ካሉ በኋላ ከዚህ በተጨማሪ ያለፈቃዳችን እየተቆረጠብን ያለው የኢች አይ ቪ መዋጮም እንዲቆም ጠይቀዋል። መምህራኑ አገዛዙ በታህሳስ ወር የቆረጠብንን ገንዝብ ከመለሰ ወደ ስራ ገበታችን ተመልሰን ቀሪዉን ገንዘብ እንዲመልሰልን እየሰራን ጥያቄዉን ማቅረብ እንችላለን ካሉ በኋላ ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን የስራ ማቆም አድማዉን እንደገና እንጀምራለን ብለዋል። በስራ ማቆም ሳቢያ በትምህርት ቤቱም ይሁን ከትምህርት ቤት ውጭ ለሚፈጠሩ ችግሮች መምህራኑ ተጠያቂዎች ያለመሆናቸውን ገልጸዋል። የዝግጅት ክፍላችን ዘግይቶ በደረሰዉ ዜና መሰረት የመምህራኑን ስራ ማቆም አድማ ተከትሎ ተማሪዎች ያለ ትምህርት በመቆየታቸዉ መስተዳድሩ የታህሳስን ወር ደሞዛቸዉን ምንም ሳይቆራጥ መክፈሉን ለማወቅ ተችሏል።መገደዱን ዘግይቶ የደረሰን ዜና ያመለክታል። በደቡብ ክልል የሚገኙ መምህራን ያለፈቃዳቸው የሚቆረጥባቸውን ገንዘብ በመቃወም የስራ ማቆም አድማ ሲያደርጉ ይህ የመጀመሪያ ግዜ አለመሆኑ የሚታወስ ነዉ።

# አንድ ለአምስት - ከቃሊቲ ዉጭ ሌላ ቃሊቲ

ወያኔ የጫካ ዉስጥ ኑሮ በቃኝ ብሎ አዲስ አበባን ከረገጠ በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ ብዙ አዳዲስ ቃላት ተፈጥረዋል፤ አንዳንድ አብረናቸዉ ያደግናቸዉ ቃላትና የቦታ ስሞች ደግሞ እየፋፉ መጥተዉ የሌሎች ሰፋ ያሉ ሀሳቦች መግለጫ ሆነዋል። ለምሳሌ የዛሬ ሃያ አምስት አመት ኮሌጅ የጨረሰ ልጅ አባቱን ቃሊቲ መግባቴ ነዉ ብሎ ቢነግረዉ አባቱ . . . . ምንዉ ስራ አገኘህ እንዴ ብሎ ከመጠየቅ ዉጭ በልጁ አባባል በፍጹም አይደነግጥም። ዛሬ ግን "ዕድሜ ለወያኔ" ቃሊቲ ሲባል የማይደነግጥ ኢትዮጵያዊ የለም። በፋብሪካ ማዕከልነቷ ትታወቅ የነበረችዉ ቃሊቲ ዛሬ አጥሩ ዉስጥ ወያኔ አፍኖ የከተታቸዉ ሰላማዊ ዜጎች ከአጥሩ ዉጭ ደግሞ የእነዚሁ ሰላማዊ ዜጎች ቤተሰቦች የሚተራመሱበት የጭንቅና የመከራ አምባ ሆናለች። አዎ ቃሊቲ እንደ አልባኒያዋ ቡሪልና እንደ ሩሲያዋ ሳይቤሪያ ዜጎችን ለማፈንና በዜጎች ላይ ሰቆቃ ለመፈጸም ሆን ተብላ እንደገና የተፈጠረችና አለፍላጎቷ አስቀያሚ ገጽታ የተከናነበች ከተማ ሆናለች። ቃሊቲ ታሪክ ከክፋታቸዉና ከጭካኔያቸዉ ዉጭ በፍጹም የማያስታዉሳቸዉን የሩሲያዉን ጆሴፍ ስታሊንና የአልባኒያዉን ኤንቨር ሆዣን እኛ ኢትዮጵያዉያን አለዝምድናችን በግድ እንድናስታዉሳቸዉ የተገደድንባት የአምባገነንነት ተምሳሌት ናት። የሚገረመዉ ቃሊቲ ወያኔ ተሸክሞ ካመጠልን የጆሴፍ ስታሊንና ኢንቨር ሆዣ መንታ ትዝታዎች አንዷ ናት። ጆሴፍ ስታሊንና ኢንቨር ሆዣ የሩሲያንና የአልባኒያን ህዝብ እስር ቤት ዉስጥ ብቻ አልነበረም ያሰሩት፤ አንድ ለአምስት በሚሉት ማለቂያ በሌለዉ ሰንሰለታቸዉ በመኖሪያ ቤቱ ዉስጥ፤ በሚሰራበት ፋብሪካ ዉስጥ፤ በሚማርበት ት/ቤቶች ዉስጥና በተደራጀበት ገበሬ ማህበር ዉስጥ ጭምር ጭምድድ አድርገዉ አስረዉታል።

የኢትዮጵያን ህዝብ የሚረገጡትንና እንደ እንስሳ እየታሰሩ የሚገረፉበትን መንገድ ለማወቅና ልምድ ለመቅሰም አልባኒያ ድረስ የሄዱት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከአልባኒያ ይዘዉብን የመጡት ቃሊቲን ብቻ አይደለም፤ ከቃሊቲ ዉጭ ህዝብን በሰንሰለት ማስር የሚያስችላቸዉን "አንድ ለአምስት" አደረጃትም ይዘዉ መጥተዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተግባራዊ አድርገዋል። አንድ ለአምስት ወያኔ ምንም ይበለዉ ምን በግንብና በሽቦ አጥር ያልታጠረ ሰፊ እስር ቤት ነዉ፤ ወይም አንድ ለአምስት - ከቃሊቲ ዉጭ የሚገኝ ሌላ ቃሊቲ ነዉ። ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ በአንድ ለአምስት ሰንሰለት ማሰር ከጀመረ ቆይቷል። ዛሬ ወያኔ ይህንን የእነ ስታሊንን የመከራ ማራዘሚያ ገመድ ከገመደብን ከአመታት በኋላ "እንድ ለአምስትን" እንደገና ማንሳት የፈለግነዉ ጉዳዩ አዲስ ሆኖብን ሳይሆን ሁለት ነገሮች አሳስበዉን ነዉ፤ አንደኛዉ ወያኔ የ"እንድ ለአምስት" አደረጃጀትን የህብረተሰባችን መሰረት ወደ ሆነዉ ወደ ቤተሰብ ደራጃ ሲያወርደዉ በማየታችን ሲሆን፤ ሁለተኛዉ ደግሞ "እሾከን በእሾክ" እንዲሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ ዘርኝነት፤ሰቆቃና ጭቆና ለመላቀቅ ወያኔ የፈጠረዉን አንድ ለአምስት አደረጃት በመሰላልነት ተጠቅሞ እራሱን እንዲያደራጅና ለወሳኙ ፍልሚያ እራሱን እንዲያዘጋጅ ለማሳሰብ ነዉ።

ወያኔ ነገረ ስራዉ ሁሉ ከጉልበትና ከሀይል ጋር የተያያዘ ነዉ፤ ስልጣን የያዘዉ በጠመንጃ ሀይል ነዉ፤ ስልጣን ላይ የቆየዉ በጠመንጃ ሀይል ነዉ። የኢትዮጵያን ህዝብ አንድ ለአምስት እያለ የሚያደራጀዉም በሀይል እያስገደደ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብማ በወያኔ ስር መደራጀት ቀርቶ ወያኔ ድርጅቱ ብቻ ሳይሆን ወያኔ የሚባል ቃሉ እራሱ ከምድረ ኢትዮጵያ ቢጠፋ ደስታዉን አይችለዉም። የሚገርመዉ ወያኔ በዚያ ጠመንጃ በጨበጠበት እጁ የጻፈዉ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 ማንኛዉም ሰዉ ለማንኛዉም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለዉ ይላል፤ ሆኖም ይህ ህገመንግስታዊ መብት ለይስሙላ የተቀመጠ የባዶ ቃላት ክምር ነዉ እንጂ ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝብ በራሱ ፈቃድ መደራጀትም አለመደራጀትም አይችልም። ለመሆኑ ወያኔ በፍጹም በማይመለከተዉ በቤተሰብ ጉዳይ ጣልቃ የሚገባዉ ለምንድነዉ? እኛስ ኢትዮጵያዉያን ይህንን የወያኔ ጣልቃ ገብነት እንዴት አድርገን ነዉ እራሳችንን ነጻ ለማዉጣት የምንጠቀምበት?

በቅርቡ የቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ለወረዳ ሁለት የላከዉን የቤተሰብ ማቋቋሚያ ቅጽ አስመልክቶ በሰጠዉ ተጨማሪ ማብራሪያ የቤተሰብ ፖሊስ መመስረት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሶ በቤተሰብ መካካል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ማህበራዊ ችግሮች መፍትሄዉ ቤተሰብን አንድ ለአምስት ማደራጀት እንደሆነ ተናግሯል። ባለፈዉ ሳምንት አጋማሽ ላይ የወያኔ ባለስልጣኖች በዳግማዊ ሚኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዉስጥ ከየትምህርት ቤቱ ለተሰባሰቡ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች አዲሱን አደረጃጀት አስመልክተዉ በሰጡት መግለጫ በቅርቡ ወደ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ይወርዳል ብለዉ ካሉት የኮማንድ ፖስት አደረጃጀት በተጨማሪ "ትራንስፎርሜሺን ፎረም" እና "የልማት ቡድን" የሚባሉ አደረጃጀቶችም እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። የወያኔ ዘረኞች ስም እየቀያየሩ ኮማንድ ፖስት አሉት፤ "ትራንስፎርሜሺን ፎረም" ወይም "የልማት ቡድን" የሁሉም አደረጃጀት ተቀዳሚ ተግባር "አንድ ለአምስት" ተብሎ የተጀመረዉን አደረጃጀት ለማጠናከርና ለማስቀጠል ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ወይኔ ለራሱ እኩይ አላማ ሲል የጀመረዉንና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማጠቃለል ላይ የሚገኘዉን የአንድ ለአምስት አደረጃጀት ወደ "ሚሊዮኖች ለሚሊዮኖች" አደረጀጃት በመቀየር ወያኔን እሱ እራሱ በፈጠረዉ ሰንሰለት ለማሰር ከአሁን የተሻለ ግዜ የሚያገኝ አይመስለንም። "አንድ ለአምስት" ከዛሬ በኋላ ወያኔ ኢትዮጵያዉያንን የሚሰልልበት ሳይሆን ኢትዮጵዉያን የወያኔን የስለላ መረብ የሚበጣጥሱበት፤ የማይተዋወቁ የትግል ጓደኞች የሚተዋወቁበት፤ ድርጅት የናፈቃቸዉ ኢትዮጵያዉያን እራሳቸዉን ከወያኔ አፈና ነጻ ለማዉጣት የሚደራጁበት የዝግጅት ቦታ መሆን አለበት። ወያኔ አንድ ለአምስት ያደራጀዉ የመንግሰት ሰራተኞችን፤ ተማሪዎችን፤ አርሶ አደሮችንና የከተማ ነዋሪዎችን እየነጣጠለ ለየብቻቸዉ ቢሆንም የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ይህንን ወያኔ የፈጠረለትን መድረክ በመጠቀምና የወያኔን የልዩነት ግድግዳ በመሰባበር አንድ ለአምስትን የመገናኛዉና የመደራጃዉ መድረክ ማድረግ አለበት።

ወያኔ ስፍር ቁጥር የሌለዉ የአደረጃጀት አይነቶች እያመጣ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ቋጠሮ የሚቋጥረዉ እሱ ሊነግረን እንደሚፈልገዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ደህንነት ተጨንቆ ወይም ለአገርና ለህዝብ ሰላምና ዕድገት አስቦ አይደለም። ወያኔ ለህዘብ ሰላምና ደህንነት የሚያስብ ቢሆን ኖሮ ማድረግ ያለበት የኢትዮጵያን ህዝብ መብትና ነጻነት ማክበር እንጂ ኮማንድ ፖስትና አንድ ለአምስት እያለ ህዝብን በማይታይ ሰንሰለት ማሰር አይደለም። ኮሚኒስቶች ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ዜጎቻቸዉን ያሰቃዩበት "አንድ ለአምስት" አደራጃጀት አራት ሰዎች አንዱ በሌላዉ ላይ ስለላ እያካሄድ ለአምስተኛዉ ሰዉ መረጃ የሚያቀብሉበት ጓደኛን ከጓደኛ፤ ተማሪን ከአስተማሪ፤ አንዱን ሰራተኛ ከሌላዉ ሰራተኛ ጋር የሚያጋጭና በህብረተሰብ መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚያደርግ የስቃይ ሰንሰለት ነዉ። ወያኔ ይህንን የስቃይ ሰንሰለት በየቦታዉ ሲዘረጋ ከርሞ ዘንድሮ ካልጠፋ ቦታ ወደ ቤተሰብ ደረጃ እያወረደዉ ይገኛል። ፓርላማዉን ጨምሮ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን፤ መከላከያዉን፤ ደህንነቱንና የአገሪቱን የኤኮኖሚ መዋቅር ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠረዉ ወያኔ ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎት ፈጣሪ ለአባትና ለእናት የሰጠዉን ብቸኛ ሀላፊነት የራሱ ለማድረግ አንድ ለአምስትን በየቤተሰቡ ለመዘርጋት እየሞከረ ነዉ።

"ፈጣሪ ሊያጠፋዉ የፈለገዉን ያሳብደዋል" ተረት ወያኔን በትክክል የሚገልጸዉ የአባቶቻችን ተረት ነዉ። በእብደት ቢባል፤ በጭቆና፤በዘረኝነት፤ በትዕቢት፤ ወይም ህዝብን በመበደልና አገር በመበተን አገራችን ኢትዮጵያ ከወያኔ የባሰ እብድ በፍጹም ሊመጣባት አይችልም። ይህ ለይቶለት ያበደ ስርዐት የአንድ ለአምስት አደረጃጀትን ብቻ ሳይሆን ካሁን በኋላ የሚወስዳቸዉን ማንኛዉም አይነት እርምጃዎች የኢትዮጵያ ህዝብ እራሱን ከባርነት ነጻ ለማዉጣት መጠቀም መቻል አለበት። ወያኔ በጠመንጃ ሀይል ከቀማን መብቶች አንዱ የመደራጀት መብት ነዉ፤ ሆኖም ለራሱ በሚያመች መንገድ አንድ ለአምስት እያለ እያደራጀን ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን የወያኔን አንድ ለአምስት አደረጃጀት ተጠቅሞ እራሱን ለማደራጀትና ከወያኔ የአፈና ሰንሰለት ለመላቀቅ አመቺ አጋጣሚ ተፈጥሮለታል። ወጣቱ፤ገበሬዉ፤ሠራተኛዉ፤ አስተማሪዉና የከተማ ነዋሪዉ ማህበረሰብ የየራሱን የጎበዝ አለቆች እየመረጠ ወያኔን እራሱ በገመደዉ ገመድ ማሰር ካለበት ግዜዉ አሁን ነዉ።

ከፋሺስት ጣሊያን ወረረ አገራችንን ያዳኗት ጀግኖች አባቶቻችን መሪ የለንም ብለዉ ጠላትን ዝም ብለዉ አልተመለከቱም። እነ በላይ ዘለቀ፤ አብዲሳ አጋና ጃገማ ኬሎ የጎበዝ አለቃ መርጠዉ እራሳቸዉን አደራጅተዉ ነዉ አገራችንን ከአደጋ ያዳኗት። በአምስቱ የትግልና የአርበኝነት ዘመን በትጥቅ፤ በቁሳቁስና በዘመናዊነት የሚበልጣቸዉን የፋሺስት ጣሊያን ጦር አሳፍረዉ ወደመጣበት የመለሱት አባቶቻችን ለድል የበቁት ፋሺስት ጣሊያን በፈጠረዉ የድርጅት መዋቅር ዉስጥ እራሳቸዉን አደራጅተዉ ነዉ። አብዲሳ አጋ ጣሊያንን ያርበደበደዉ በጣሊያን ተራሮችና በረሃዎች ዉስጥ ነዉ። ዘርዓይ ደረስ የጣሊያኖችን አንገት የቀላዉ በሮም አደባባዮች ዉሰጥ ነዉ። ዛሬ በወያኔ ጥቁር ፋሺስቶች እየተገዛ ቁም ስቅሉን የሚያየዉ ኢትዮጵያዊ የእነዚህ ጀግኖች የልጅ ልጅ ነዉና የአባቶቹን ታሪክ በመድገም ወያኔ በፈጠራቸዉ ድርጅቶች ዉስጥ እየተደራጀ እራሱን፤ አገሩንና ወገኑን ነፃ ማዉጣት አለበት።

ወያኔን በህዝባዊ አመጽም ሆነ በህዝባዊ እምቢተኝነት ወይም በሁለቱም የትግል ስልቶች ታግሎ አገራችንን ነጻ ለማዉጣት ከዉጭ የሚመጣ ሀይል የለም፤ ነጻ አዉጪዉም በሚገኘዉ ነጻነት ተጠቃሚዉም ያለዉ እዚያዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ነዉ። ነፃነት ያለትግል ትግል ደግሞ ያለ ድርጅት በፍጹም የሚታሰቡ ነገሮች አይደሉም። ከአላማ ጽናት ቀጥሎ አንድ ህዝብ ነፃኑቱን እንዲጎናጸፍ የሚያስችለዉ ድርጅታዊ ብቃቱ ነዉ፤ ወያኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሱ ፈቃድና ፍላጎት ዉጭ እንዳይደራጅ አጥብቆ የሚታገለዉ ይህንን ሀቅ በሚገባ ስለሚረዳ ነዉ። ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ለመቀዳጀት መታገል ለመታገል ደግሞ ወያኔ ፈቀደም አልፈቀደ ህዝብ በመረጠዉና ይበጀኛል ብሎ ባሰበዉ መንገድ ሁሉ መደራጀት አለበት። የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ሰላዮችና ካድሬዎች ተከብቦ እንደሚኖር የታወቀ ነዉ፤ ሆኖም ይህንን ከበባ ጥሶ ለመዉጣት ወያኔ እራሱ ያመቻቸዉ መንገድ አለ፤ እሱም ከሰራተኛና ከገበሬዉ ተነስቶ ቤተሰብ ድረስ የወረደዉ የወያኔ "አንድ ለአምስት" አደረጃጀት መዋቅር ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት 35 አመታት በሁለት አምባገነን ስርዐቶች ዉስጥ አልፏልና ስለአምባገነኖችና ስለ አምባገነንነት ብዙ ልምድ አለዉ። ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድ ወጥ በሆነ ድርጅታዊ መዋቅር ዉስጥ የሚያደራጀዉ የህዝብን ስነ ልቦና ለመስበርና ህዝብ በፍርሀት ደመና ተዉጦ እየሰገደ እንዲኖር ለማድርግ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የወያኔን ማንነት በሚገባ የተረዳዉ ስለሆነ የተገነባ ሞራል ያለዉና በራሱ የሚተማመን ህዝብ ነዉ፤ ስለሆነም ወያኔ የፈጠረዉን የድርጅት ጋጋታ እራሱን ነፃ ለማዉጣት ይጠቀምበታል የሚል ሙሉ እምነት አለን። ያለፈቃዳቸዉና ያለ እምነታቸዉ በግዴታ በአንድ ለአምስት ከተደራጁ ሰዎች ከአስር ዘጠኙ ወያኔን የሚቃወሙና የወያኔን ስርዐት ለማፍረስ የሚታገሉ ሰዎች ናቸዉ። እነዚህ ሰዎች ወያኔ ለስለላና ለጭቆና ያዋቀረውን የ"አንድ ለአምስት" አደረጃጀት ወያኔን እራሱን ለመታገልና ብሎም ለማዳከም እንደ መሣሪያ ተጠቅመዉ ይህንን አስከፊ ስርዐት ከጀርባቸዉ ላይ አንከባልለዉ መጣል አለባቸዉ።

## መብራት ኃይልን የከበበዉ የሙስና ደመና 500 ሚሊዮን የአገርና የህዝብ ገንዘብ ግለሰቦች ኪስ መክተቱ ተሰማ

በኢትዮጵያ ኤለክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ውስጥ በነገሰው ከፍተኛ የሙስና ወንጀል የኢትዮጵያ ህዘብ ካዝና ዉስጥ መግባት የነበረበት ከግማሽ ቢሊዮን ባላይ የሚጠጋ የህዘብና የአገር ገንዘብ ወደ ወያኔ ባለስልጣኖችና ቤተሰቦቻቸዉ ኪስ መግባቱን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸዉ የአገር ዉስጥ ምንጮች ገለጹ። የኢትዮጵያ ኤለክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ ገንዘብ የተመደበላቸዉን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የሚያንቀሳቅስ መ/ቤት ሲሆን የወያኔ ባለስልጣኖች በፕሮጀክት ስም ከዉጭ ምንጮች የሚገኘዉን ገንዘብ ገና አገር ቤት ከመግባቱ በፊት እዚያዉ ባህር ማዶ ባለዉ የባንክ ሂሳቸዉ ዉስጥ እንደሚያስገቡት ታዉቋል። ኮርፖሬሺኑን ለረጂም ግዜ በዋና ስራ አስኪያጅነት የመሩትና ይህንን ሰፋ ያለ የሙስና አሰራር አጽንተዉ የተቃወሙት አቶ ምህረት ደበበ በቅርቡ ግምገማ ተደርጎባቸዉ ከስልጣናቸው የተነሱት የወያኔን ሙስና ፊት ለፊት በመቃወማቸዉ እንደሆን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ።

ህወሃትን ከበረሃ ድረስ አቅፎ የመጣዉና የደህንነት ምክትል ሃላፊ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ በም/ል ጠቅላይ ሚኒስትር ማእረግ የኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና የመብራት ሃይል ኮርፖሬሺን ቦርድ ሰብሳቢ የሆነዉ ደብረ ጽዮን ገብረ የአቶ ምህረት ደበበን ከሃላፊነት መነሳት አስመልክቶ በሰጠዉ አስተያየት "ምህረት ደበበ የሚመሰገነዉን ያክል ጉድለትም እንደነበረበት ይረዳል፤ ከሃላፊነቱ ሲነሳም አልደነገጠም" ማለቱ የሚታወስ ነዉ። አማካሪና የቦርድ ሊ/መንበር መሆን ቀርቶ ቢመክሩት እንኳን ምክር የማይገባዉ ደብረጺዮን አቶ ምህረት ደበበ በብቃት ችግር እንደተነሱ አድርጎ ለመናገኛ ብዙህን ቢገልጽም፣ አቶ ምህረት ደበበ ግን በህወሃት ባለስልጣናት ስውር እጅ ሲቀነባበር የነበረውንና ኢትዮጵያን ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ እንድታጣ ያደረገውን ከፍተኛ ሙስና ሲቃወሙ እንደነበር ለጠቅላይ ሚ/ር ሃይለማርያም ደሳለኝ የቀረበው እና ለኢሳት የደረሰው የጸረ ሙስና ኮሚሽን የምርመራ ሪፖርት ያስረዳል።

በ1999 እና በ2000 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የኤሌክትሪክ ኃይልን ተደራሽ ለማድረግ የሚረዱ ትራንስፎርመሮችን ለመግዛት ካወጣቸው አለም አቀፍ ጨረታዎች ጋር ተያይዞ በጨረታዎቹ ሂደት ላይ ግልጽነትና ኃላፊነት የጎደለው አሰራር መከሰቱንና ይህም የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማዳረስ በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምርመራ በማድረግ የምርመራ ውጤቱን ለቀድሞዉ በወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትት መለስ ዜናዊ ማቅረቡ የሚታወስ ነዉ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን አገር አቀፍ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ፕሮግራምን ተደራሽ ለማድረግ ያግዛሉ በማለት የሥርጭት ትራንስፎርመሮችን ለመግዛት ሁለት ዓለም አቀፍ ጨረታዎችን በ1999 እና በ2000 ዓም ሲያወጣ ሁለቱንም ጨረታዎች "ጉድላክ እስቲል ቲዩብስ ሊሚትድ" የተሰኘ የሕንድ ኩባንያ ማሸነፉ በወቅቱ ተነግሯል። ሆኖም ኩባንያው የጨረታው አሸናፊ ተብሎ ይለይ እንጅ ባቀረበው ሰነድ ላይ የገለጸው የትራንስፎርመር ዓይነት ኮርፖሬሽኑ በጨረታው ሰነድ ላይ ሊገዛው ካሰበው ዓይነት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ሳይገኝ ቀረ። ይህ ያልተጠበቀ ክስተት በግዥ ሂደቱ ውስጥ ገና ከጅምሩ የሙስና ወንጀል ድርጊት የተጠነሰሰ መሆኑን በወቅቱ ብዙዎች የተናገሩ ቢሆንም ጨኸታቸዉ ሰሚ ሳያገኝ ቀርቷል።

"ጉድላክ ስቲል ቲዩብስ ሊሚትድ" ያቀረባቸው ሰነዶች ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ያወጣውን መስፈረት እንደማያሟሉ ሲታወቅ ፣ ኩባንያ ያቀረበው ትራንስፎርመር በኮርፖሬሽኑ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠው መስፈርት (ስፔስፊኬሽን) አያሟላም በሚል በአሰራሩ መሰረት በቴክኒክ ግምገማ ውድቅ ማድረግ ነበር፤ ሆኖም የኮርፖሬሺኑ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ምህረት ደበበ ጨረታዉ ዉድቅ እንዲሆን ከፈተኛ ተቃውሞ በማሰማት ላይ እያሉ የኮሚቴ አባላቱ ተቃውሞውን ወደ ጎን በመተውና አዲስ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ኩባንያው የጨረታ ግዴታቸዉን አሟልተዉ ከቀረቡ ሌሎች ኩባንያዎች ጋር እንዲወዳደር በማድረግ በህገወጥ መንገድ ቀጣዩን የ ፋይናንስ ግምገማ ሥርዓት እንዲያልፍ አድረጉ። በዚህ አግባብ ኮርፖሬሽኑን ወክለው በጨረታው የተሳተፉ አካላትም ሆነ ጨረታውን አሸነፈ የተባለው ኩባንያ ባለቤት በኪራይ ሰብሳቢነት ስሌት ያልተገባ ጥቅም ለመቀራመት እየተንደረደሩ መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት አሁንም ለቀድሞዉ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢቀርብም እሱም ቢሆን የሙስናዉ ተካፋይ ነበርና የጨረታው ሂደት ቀጥሎ ኮርፖሬሽኑ እና የጨረታው አሸናፊ ኩባንያ በሚቀርቡ የትራንስፎርመሮች መጠንና በገንዘብ ጉዳይ ላይ ውል የሚዋዋሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዉ አገሪቱን ባላገኘችዉ ጥቅም ባለዕዳ አድረገዋትል።

ጨረታዉን በቅርብ ሆነዉ የሚከታተሉትና የወያኔ ባለስልኖች በግዥው ሂደት ውስጥ የማይገባ ጥቅም ለራሳቸውና ለኩባንያዎቹ ባለቤቶች ለማስገኘት በማሰብ በዋና ወንጀል አድራጊነትና በልዩ ተካፋይነት በሚፈፀም ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸው ተመልክቷል። በድርጊቱ ውስጥም በስልጣን ያለአግባብ መገልገል፣ የመንግስት ስራን በማያመች አኳኋን በመምራት እና ከባድ አታላይነት የሙስና ወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙ መሆናቸው ታይቷል። በዚህ አግባብ በተፈጸሙ ብልሹ አሰራሮች ሳቢያ በአገር ጥቅም ላይ ከ26 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይም ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ጉዳት መድረሱም ተጠቅሷል። ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በሰባት የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች፣ በአራት የጨረታ ኮሚቴ አባላትና የ"ጉድላክ" እና የ"ኩብራ" ኩባንያ ባለቤቶች ላይ ተገቢውን ማስረጃዎች አሰባስቦ በሁለት የክስ መዝገቦችና በስድስት ክሶች በማጠናቀር ጉዳዩን ለመጀመሪያ ጊዜ ሐምሌ 3 ቀን 2005 ዓ.ም ጉዳዩን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቧል። የአቶ ምህረት ደበበ የስልጣን ዝውውር የጀርባ ፍጥጫ ሌላው የግምገማ ታሪክ ይህን ሲመስል፣ በተፈጠረው አለመግባባት ስራውን በአግባቡ እንድመራው በወጣው ህግ እና ደንብ መመራት አልቻልኩም ሲሉ ያቀረቡት መልቀቂያ ጥያቄ በዶ/ር ደብረጺዮን ገብረሚካኤል ተቀባይነት አግኝቶ ምንም በቂ ሃላፊነት ወደ ሌላው የጠቅላይ ሚ/ሩ አማካሪነት እንዲዛወሩ ተደርጓል።

በቅርቡ ከሃላፊነታቸዉ የተነሱት አቶ ምህረት ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ያደረጉትና የሙስናውን ድራማ ከጀርባ ሆነው ሲመሩት የነበሩት ዋና ዋናዎቹ የህወሀት ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር ሳይውሉ፣ ብዙም ስልጣንና ሃላፊነት ያልነበራቸዉ ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸዉ በትክክል የሚያሳየዉ የወያኔ ስርዐት ሆን ተብሎ በሙስና ለመክበር የተቋቋመ ስርዐት መሆኑን ብዙ የፖለቲካ ተቺዎች በመናገር ላይ ናቸዉ።

## ኢትዮጵያ የአፍሪካ የጉዲፈቻ ማዕከል መባሏ ተሰማ

በቅርቡ ግዜ ይፋ የሆኑ አለም አቀፍ መረጃዎች በግልጽ እንደሚያሳዩት ባለፉት 6 ዓመታት ዉስጥ ከአፍሪካ አህጉር በጉዲፈቻ ስም ወደ ውጭ ከተላኩት 34 ሺ 342 ህጻናት ውስጥ 63 በመቶ ወይም 21 ሺ 365 ህፃናትን በመላክ ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ አገር መሆና ታወቀ። ከጉዲፈቻ ድለላና የስራ አፈጻጸም የሚገኘዉ ገንዝብ እጅግ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ድረስ እየሄዱ የጉዲፈቻ ድለላ ስራ ፈቃድ የሚጠይቁ ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መሄዱን የሚኒስቴሩ መ/ቤት ሰራተኞች ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ የጉዲፈቻ ስራ የሚሰራዉ እንደ ሌሎች አገሮች ወላጅ አልባ የሆኑ ህጻናትንና ማሳደግ የሚፈልጉ ቤተሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት ሳይሆን ለጥቅምና ለገንዘብ ስለሆነ በአብዛኛዎቹ ለጉዲፈቻ በሚቀርቡ ህፃናት የህይዎት ታሪክ ላይ የሚጻፈው " ተጥለው የተገኙ ወይም ወላጆቻቸውን በህይዎት ያጡ " የሚል በመሆኑ በልጆቹ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዳሳደረ ለማወቅ ተችሏል።

የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር የሆኑት ወ/ሮ ዘነቡ መንግስት ህጻናቱን ወደ ውጭ ለማላክ ፍርድ ቤት የሚያስከፍለው 25 ብር ብቻ መሆኑን ይናገሩ እንጅ፣ የጉዲፈቻ አሳዳጊዎች፣ አንድ ህጻን ለማግኘት እስከ 20 ሺ ዶላር እንደሚከፍሉ ይናገራሉ።የደቡብ ክልል የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት ወ/ሮ መሰረት መስቀሌ ደግሞ በበኩላቸዉ በህፃናት የሚነግዱ አካላት በርካታ መሆናቸውን ይገልጹና ኢትዩጵያ ያወጣችው አማራጭ የህፃናት መመሪያ በራሱ ሙሉ አለመሆኑንና ለችግሩ መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉንም ይናገራሉ። በርካታ የፖሊስ እና የመንግስት አካላት " ህጻናት ወደ ውጪ ቢሄዱ ይለወጣሉ" የሚል አመለካከት መያዛቸው ስህተት ነው የሚሉት ሃላፊዋ፣ በደቡብ ክልል እንደወጡ የቀሩ ልጆቻቸዉን የሚጠብቁ እናቶች ዛሬም መንግስትን እያማረሩ ነው ብለዋል ።ኢቲቪ በቅርቡ ባቀረበው ዘገባ 832 ህጻናት በየአመቱ ከኢትዮጵያ ይወጣሉ ብሎ የዘገበ ሲሆን ከፌደራል መደበኛ ፍርድ ቤት የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በ2005 ብቻ 2 ሺ 201 ህጻናት ከአገር እንዲወጡ ፈቃድ ተሰጥቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## አስራ ስምንት አመት ሙሉ ታምኖበት ሲሰራበት የቆየዉ ህግ ህገመንግስታዊ አይደለም ተባለ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር የነበረዉ መላኩ ፈንታ ዬኔ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤት መታየት የለበትም ሲል ያቀረበዉን አቤቱታ ለመስማት የተቀመጠዉ የፌዴሬሺኑ ምክር ቤት ላለፉት 18 ዓመታት በስራ ላይ የነበረውና የቀድሞዉን ጠ/ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔን ጨምሮ የተለያዩ ባለስልጣናት ጉዳይ የታየበትን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8 ተራ ቁጥር 1 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7 ተራቁጥር 1 ሕገመንግስቱን እንደሚጥሱ በመወሰን የመላኩ ፈንታን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን ከአዲስ አበባ የደረስን ዜና አስረዳ።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 15ኛ ወንጀል ችሎት በሙስና ወንጀል የተከሰሱት አቶ መላኩ ፈንታ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር በነበሩበት ጊዜ በሚኒስትር ማዕረግ ሆነው ሲሰሩ ስለቆዩ የተከሰሱበት ጉዳይ መታየት ያለበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ነው ወይስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚለው ጭብጥ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በሃላ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8-1 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7-1 የህገመንግስቱን አንቀጽ 20-6 ይጥሳሉ ወይስ አይጥሱም የሚለው ነጥብ ሕገመንግስታዊ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔና ለምክርቤቱ በመራው መሠረት ጉዳዩ የፌዴሬሽን ምክርቤትን አባላትን ለሁለት ከፍሎ ሲያከራክር ከቆየ በኋላ ዉሳኔ ተሰጥቶበታል።

በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት የሕገመንግስት አጣሪ ጉባዔ ጉዳዩን መርምሮ እነመላኩ ፈንታ ያነሱት ጭብጥ የህገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ውሳኔ ካሳለፈ በኃላ ከትላንት በስቲያ እና በትናትናው ዕለት በምክርቤቱ የሕገመንግስትና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ የደረሰበትን የውሳኔ ሃሳብ በዛሬው ዕለት ለፌዴሬሽን ምክርቤት አቅርቧል።

በውሳኔ ሃሳቡ ላይ እንደተመለከተው የህገመንግስት አጣሪ ጉባዔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 84 እና በአዋጅ ቁጥር789/2005 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተመራለት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ ሰዎች የመንግስት ባለስልጣን በመሆናቸው ብቻ ከሌሎች ተለይተው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ክሳቸው እንዲታይ ማድረግ የህገመንግስቱን አንቀጽ 20 -6 ማለትም ይግባኝ የማቅረብ መብትን ስለሚጥስ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ወንጀል ድርጊት የተከሰሱ ሰዎች መካከል አንዱ የይግባኝ መብት እንዲያገኝ ሌላው ይህን መብት እንዳያገኝ የሚፈቅድ ሕግ በመሆኑ፣ በተጨማሪም የህገመንግስቱ አንቀጽ 25 ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ናቸው ፤በማናቸውም ሁኔታ በመከሰሳቸው ልዩነት አይደረግም የሚለውን የህገመንግስት ድንጋጌ መጣስ ስለሚሆን የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8-1 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7-1 ድንጋጌዎች በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9-1 ማለትም ሕገመንግስቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ መሆኑን የሚያሳውን ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል።

በዚህ መሰረት ቋሚ ኮምቴው ከአጣሪ ጉባዔውና በጹሑፍ ከቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በተጨማሪ የጉባዔው አባላት ቀርበው ለቋሚ ኮምቴው እንዲያስረዱ ተደርጎ ቋሚ ኮምቴው በጉዳዩ ላይ በቂ ውይይት ካደረገ በሃላ የውሳኔው ሃሳብ በአብላጫ ድምጽ እንደተቀበለው ታውቋል።ምክርቤቱ ዛሬ በጉዳዩ ላይ በተወያየበት ወቅት ምክርቤቱን ለሁለት የከፈሉ ሃሳቦች ተንሸራሽረዋል። በተለይ አቶ መላኩ ፈንታ ያቀረቡትን ጥያቄ ትክክለኝነቱን በማረጋገጥ የተሚገቱ ወገኖች እንዳስረዱት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8(1) ባለስጣናት ከስራ ጋር በተገናኘ ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ ጉዳያቸው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚታይ እንደሚደነግግ፣ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7(1) በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንኑ ድንጋጌ እውቅና እንደሚሰጥ፣ በተለይ አዋጅ ቁጥር 25/88 ከወጣ 18 ዓመታት የቆጠረ መሆኑን በማስታወስ በዚህ ሕግ የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔን ጨምሮ ሌሎች ባለሰልጣናት ጉዳያቸው የታየበት እንደነበር አስታውሰዋል።

## ሐቁ ተሰደደ!

ትናንትሽን ከአድማስ ማዶ
ባዕድ ሀገር ማንስ ወዶ

እኔና እናንተ እኮ ከአመታት በፊት
በታሪክ በሃይማኖት በባህል በትውፊት

በጋሻና በጦር ጀብደኛ ባለሀገር
የአንድ አያቶች ዘር የአንድ አፈር ሰፈር

ግና ዛሬን ይኸው ይከፋፍሉናል
እራስን ከፍ አርገው ትንሾች ይሉናል

በስልጣን ከፍ ከፍ
በሃብትም ከፍ ከፍ
የወደቁ ለታ ማንነት እንዳይተርፍ

ትንሹ ነብዩ በጥይት ተገድሎ ያላንዳች ጥፋቱ
ያለ ፍትህ ታስሮ ስንቱ ወገኔ ሞቶ ወጣት አዛውንቱ
ይሄ ሁሉ ጥፋት ፍትህ አልባነቱ
የየኔ ሰው ገብሬ በእሳት መሞቱ

የሐረሩን እንቡጥ ተስፋችን የነገው
ቀጥቅጥጠው ገደሉት ባልዋለበት ውለው
እስክንድር ፤ አንዱአለም ፤ ናትናኤል ፤ ርዕዮት አለሙ
ያለ ምንም በደል በግፍ የታሰረው ክርስቲያን ሙስሊሙ

ፍትህ ቢጎድልበት ተገፍትሮ የወጣው
በሳውዲ አረቢያ ደሙ ለፈሰሰው
የወገኔን እንባ ወገኑ አበሰው
ይብላኝ ለወያኔ ቀኑ ለደረሰው

ማዳመጥ አይሻ ተቃዋሚ አፍርሶ
እኔ ብቻ አዋቂ ጭራሽ ተኮፍሶ

በአኬልዳማ ሸብር ህዝብ እያሳደደ
ውሸት ተደላድሎ ሐቁ ተሰደደ::

ምንድን ነው ነፃነት?
ባርነት ምን ሲባል ብለው የታገሉት
ለነፃነት ብለው ህዝብ ላይ ጉብ ያሉት
አዋቂ ነን ብለው ታሪክ ያጎደፉት

ከዚህ መልስ ኦሮሞ
ከዚያ መልስ ጋሞ
ከዚህ መልስ ሲዳማ
ከዚያ መልስ ኩናማ

አንድነት በትነው
ህጉን አፈራርሰው
ክፍፍልን ዘርተው

ይሄ ነው ነፃነት ስንቱ የሞተለት?

ይበቃል ከእንግዲህ ጨለማ አንፈልግም
ብትደበዝዝ እንጂ እውነት ጠፍታ አታውቅም:: (2x)

ከሀና ሰመረ (ኖርዌይ)